ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

“ሚስጥሩ” ቴአትር ከመድረክ ግንባታ ዕሳቤ አንፃር

በ

ሙሉ በላይ

ግንቦት 2015 ዓ.ም

ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

“ሚስጥሩ” ቴአትር ከመድረክ ግንባታ ዕሳቤ አንፃር

በ

ሙሉ በላይ

የጥናቱ አማካሪ

ረ/ፕ ወርቁ ሙሉነህ

በመህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰበ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ።

ግንቦት 2015 ዓ.ም

የ አ ማካ ሪ ው ማረ ጋ ገ ጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።የአማካሪው ስም_____

ፊርማ _____

ይህ በተማሪ ሙሉ በላይ "ሚስጢሩ ቴአትር ከመድረክ ግንባታ ዕሳቤ አንፃር " በመተንተን የቀረበ የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን የዩኒቨርስቲውን ጥራት ደረጃ ያሟላና በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው።

ፈታኝ አንድ _____ ፊርማ _____

ፈታኝ ሁለት _____

ፊርማ _____

ቀን_____

ምስጋና

በቅድሚያ ሁሉን ላሳካው ለድንግለ ልጅ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋናዬን አቀርባለውሁ ። ለጭንቅ አማላጅቷ እናቴ ኪዳነ ምህረት አመሰግንሽ ዘንድ ምክንያቴ ብዙ ነው ። በምቀጠል ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ እንዲሁ መስራትና ከግብ ማድረስ እንዳሚችል ላገዘኝ ረ/ፕ ወርቁ ሙሉነህ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። በተጭማሪም ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ስሰራ ላገዙኝ ለወዳጅ ጓደኞቼ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለው ።

አ ጠ ቃ ሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የተሰራ ጥናት ነው ። “የ ኪነ-ህንፃ ለቴአትር መድረክ ያለዉን አስተዋፆ በሚስጢሩ ቴአትር አስረጂነት መተንተን ላይ ያቶከር ነው ። በመሆኑም የኪነ-ህንፃ ጥበብ ለቴአትር መድረክ ያለውን አስተዋፆ በሚስጢሩ ቴአትር አስረጂነት ግምገማ ይሰጣል ። አጥኚው በምልከታ ፣ ቃለ መጠየቅ በማድረግ እና የተለያዩ መፀሀፍቶችን በመጠቀም የሚስጢሩን ቴአትር መድረክ ፣ ከመድረክ ግንባታ ፅሳቤ አኳያ አንፃር የገመገም ሲሆን የመድረክ ግንባታው የግዜና የወቅቱ አገላለፅን ከታሪኩ ጋር አብሮ አለመሄዱንና ወቅቱን አለመግለፁ አስተዉሎባቿል ።

የአማካሪውመሚጋገጫ I
ምሺጋና II
አጠቃሎ III
ምዕራፍ አንድ 1
1. መግቢያ 1
1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ 2
1.2.1 የጥናቱ ዓብይ ዓላማ 2
1.2.2 የጥናቱ ንዑስ ዓላማ 2
1.3 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች 2
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ 3
1.5 የጥናቱ መጠነ ራዕይ 3
1.6.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ 4
1.6.1.1 ግላዊ ምልከታ 4
1.6.1.2 ቃለ መጠይቅ 4
1.6.1.3 የሰነድ ትንተና 5
1.7 የጥናቱ አወቃቀር 5
1·8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው 6
ምዕራፍ ሁለት 7
2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት 7
2.1.2 ኪነ-ህንፃ ማለት ምን ማለት ነው? 7
2·1·2 የኪነ-ህንፃ ታሪካዊ ዳራ 8
2·1·5 የመድረክ ምንነት 9
2·1·6 የመድረክ ግንባታ ታሪካዊ ዳራ 9
2·1·7 የመድረክ አይነቶች 10
2·1·7·1 የፊትለፊት መድረክ 10

2·1·7·2 ባለ ሶስት ጎን መድረክ 11
2·1·7·3 ክብ መድረክ 12
2·1·7·4 አካባቢያዊ መድረክ 13
2·1·8 የመድረክ መሰረታዊ ትርጉሞች 14
ምዕራፍ ሶስት 16
3.1 የመረጃ ትንተና 16
3.1 .2 የሚስጢሩ ቴአትር የመድርክ ግንባታ 17
የፊትለፊት መድርክ ስዕል 18
3.1.3 የሚስጥሩ ቴአትር የምድረክ ግንባታ አጠቃላይ ዳሰሳ 19
3.1.4 የሚስጥሩ ቴአትር መድረክ ግንባታ ደካማ ጎን 20
3.1.5 የሚስጥሩ ቴአትር መድርክ ግንባታ ጥሩ ጎን 20
ምዕራፍ አራት 22
4.1 ማጠቃለያ 22
4.2 የመፍትሄ ሀሳብ 22
ዋቢ መጻሃፍት 26

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

ቴአትር የሰው ልጆችን በህይወት ዘመናቸው የሚያጋጥማቸውን ከግዜ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ስሜቶቻቸውን በተለያየ መልኩ መድረክ ላይ የሚቀርብበት የኪነ-ጥበብ ዘርፍ ነው:: ቴአትር ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ፣ህይማኖታዊ፣ ስነምግባራዊ እና ስነ-ልቦናዊ አስተሳሰቦችን በአንድ በተወሰነ ቦታ እና ግዜ በመድረክ ላይ በማሳየት በሰዎች አመለካከት እና አስተሳሰብ ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጣ ጥበብ ነው፡፡ አንድ ቴያትር መድረክ ላይ ከመዘጋጀቱ በፊት በዋናነት የመድረክ ግንባታ እንዴት እንደሚገነባ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ እናም ከመድረክ ገንባታ ጋር የሚሄድ ቁሳቁስ፣ መብራት፣ አልባሳት እናም ሌሎችም ለዝግጅት ወይም ለግንባታ የሚረዱ ሂደቶችን ለማካተት ቴአትሩ ህይወት ዘርቶ በመድረክ ላይ እንዲቀርብ የሚያደርግ የቡድን ስራ ነው ፡፡ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ‹‹ሚስጥሩ›› ቴአትር በአለህኝ ብርሃኔ ተደርሶ በተስፋዬ ገ/ማርያም ተዘጋጅቶ በብሄራዊ ቴያትር በ2015 ዓ.ም በመታየት ላይ የሚገኘው ቴያትር ከመድረክ ግንባታ ዕሳቤ አንፃር ሰፊ ማብራሪያ በመስጠት በተገቢው መንገድ መገንባቱን እና መዘጋጀቱን የሚያጠና ነው፡፡

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ እንዲሰራ ያነሳሳው ዋነኛው ምክንያት የኪነ-ህንፃ ጥበብ ለቴአትር መድረክ ግንባታ ያለው ፋይዳ በ‹‹ሚስጥሩ›› ቴአትር አስረጂነት ምን ይመስላል የሚለውን በጥልቀት ተንትኖ ለተደራሽ ማቅረብ ወይም ማድረስ ሲሆን፡፡ በተጨማሪም የ‹‹ሚስጢሩ›› ቴአትር የተሰኘው ከመድረክ ግንባታ ዕሳቤ አንፃር የሚጠበቅበትን የመድረክ አገነባብ ሁኔታ አሟልቷል ወይ? መድረኩ ከቴአትሩ ታሪክ ጋር ተዛምዶነት አልው ወይ ፤ ስንል በመድረክ ላይ የምንጠቀምባቸውን የኪነ-ህንፃ ጥበብ አላባዊያን እና የመድረክ ግንባታ ህጎችን አካቷል ወይ? ደካማ እና ጥሩ ጎኑን በማንሳት ቴአትሩ በመድረክ ላይ መቅረቡና ለቴአትሩ መድረክ መገንባቱስ ምን አስተዋጽዖ አበርክቷል የሚለውን በጥልቀት በመዳሰስ መረጃን ለመስቀመጥ ብሎም ፋይዳውን ለተደራሽ ማድረስ፡፡

1.2. የጥናቱ ዓላማ

አጥኚው ጥናታዊ ፅሁፉን አብይ እና ንዑስ በማለት በሁለት መንገድ ተመልክቶታል።

1.2.1 የጥናቱ ዓብይ ዓላማ

❖ የ‹‹ሚስጢሩ›› ቴአትር ለቴአትር መድረክ ግንባታ ያለውን አስተዋፆ በ‹‹ሚስጥሩ›› ቴአትር አስረጂነት መተንተን ላይ ያቶከረ ነው ።

1.2.2 የጥናቱ ንዑስ ዓላማ

➢ የ‹‹ሚስጢሩ›› ቴአትር የመድረክ ግንባታ እና አጠቃቀም እንዲሁም ከዘውጉ ጋር የሚሄድ የመድረክ አገነባብ፣ ቀለም፣ አልባሳት ቁሳቁስ እናም መብራት ምን እንደሚመስል ማጥናት ነው።

➢ የ‹‹ሚስጢሩ›› ቴአትር በመድረክ ላይ ሲታይ የመድረክ ግንባታውን ደካማ ጎኑን እና ጥሩ ጎኑን መለየት ።

➢ የኪነ-ህንፃ ጥበብ ባይኖር የቴአትር መድረክ ውበቱ እስከምን ድረስ ነው ?

መኖሩስ አስተዋፆ ለቴአትር መድረክ አበርክቷል? የሚለውን መለየትና መተንተን ።

1.3 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- የ‹‹ሚስጢሩ›› ቴአትር መድረክ ከመድረክ ግንባታ ዕሳቤ አንፃር ደካማና ጥሩ ጎኑ ምንድ ነው?
- የ‹‹ሚስጢሩ›› ቴአትር የመድረክ ግንባታ ከታሪኩ ጋር እንዴት ተዛምዷል?
- የኪነ-ህንፃ ምንነት እና የኪነ-ህንፃ መሰረታዊ አላባዊያን የምንላቸው የትኞቹን ፍሬ ነገሮችን ነው?
- የኪነ-ህንፃ ጥበብ ለቴአትር መድረክ ያለው አስተዋፆ ምንድንነው?
- የቴአትር መድረክ ግንባታ ከኪነ-ህንፃ አላባዊያን አኳያ እንዴት ይገመገማል?

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

አጥኚው የጥናቱን ጠቀሜታ ያለውን አስተዋፆ በዝርዝር ያስቀምጣል ልሚሳሌ ፦ ለአጥኚው ፣ለማህበረሰብ ፣በሙያው ለተሰማሩ ፣ተመሳሳይ ጥናት ለሚሰሩ ፣ እናም የሚሰጠውን ጥቅመ በዝርዝር አስቀምጧል ።

ጥናቱን ለመስራት አጥኚው ስለ ቴአትር መድረክ ግንባታ የምያትቱ አያሌ ዋቢ መፀሀፍትንና የተለያዩ አለም አቀፍ ድህር ገፆችን በተገቢው መንገድ መዳሰስ ይኖርበታል። በዚህም ስለ ቴአትር መድረክ ግንባታ ብዙ እውቀትን እንዲሸምት ያደርገዋል።

ይህ ጥናት ለተመልካቹ ስለ ቴአትር መድረክ ያላቸውን እውቀት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ እና እንዲሁም ስለቴአትር መድረክ ምንነት እንዲያውቁ ያግዛል። ተጨባጭ የሆነ መረጃ ለመስጠት ይህም ሲባል የመድረክ ግንባታ ከሚሰራው ከቴአትር ታሪክ ጋር እንዴት መስራት እንዳለብንና መድረክ ስንገነባ ምን ምን ነገሮችን (ግዕባቶችን) እንጠቀማለን የሚለውን በጥልቀት በመተንተን እውቀት ማስጨበጥ ነው። ለምሳሌ ፦ መድረክ የሚያንፁ ባለሙያዎች በዙ ጥንታዊ ፁሁፍ ላይ የሚነሱትን ደካማና ጥሩ ጎኑን በመመልከት ወደፊት ለሚገነቡት መድረክ ትልቅ እገዛ ይሆናቸዋል።

የሚስጢሩ ቴአትር መድርክ ግንባታ በሚስጢሩ ቴአትር አስረጂነት ተመሳሳይ ጥናት ለሚያደርጉ ግለሰቦች መሰረት እንዲሆን እና እንደ ተዛማጅነት ይጠቀማል ።

1.5 የጥናቱ መጠነ ራዕይ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያተኩረው የቴአትር መድረክ ያለውን አስተዋፆ በ‹‹ሚስጢሩ›› ቴአትር በመድርክ ግንባታ አደረጃጀት በተሰኘው ጥናታዊ ፅሁፍ ዙሪያ ላይ ስለ ቴአትር መድረክ እና እንዲሁም በ‹‹ሚስጢሩ›› መድረክ ግንባታ ላይ ትንተና መስጠት ብቻ ይሆናል ።

1.6 የጥናቱ ዘዴ

አጥኝዉ ይህን ጥናት ሲሠራ ገላጭ የምርምር ስልትን መሰረት አድርጎ ሰርቷል ።ያለው እንግዳ አወቅ ሙሉ "የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር" በሚለው መጽሃፉ ላይ ስለ ገላጭ የምርምር ዘዴ እንደሚከተለው አስቀምጧል። "ገላጭ ምርመር ከስሙ እንደምንረዳው ተመራማሪው አንድን ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን እንደሆነ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ

በትርካዊ መንገድ የሚቀርብበት ነው። ገላጭ ምርምር በጣም ጠቃሚ የሆነ መረጃ ሊገኝበት የሚችል ጥሩ የምርምር አይነት ነው። በተለይ ወደፊት በዚያ ዙሪያ ሰፋ ያሉ ምርምሮች የሚካሄዱ ከሆነ የችግሩን መልክ ለመለየት ና የምርምሩን አቅጣጫ ለመወሰን ያስችለናል"። በምንሰራው ርዕሰ ጉዳይ ማብራራት አጥኝዉ ይህን የጥናት ዘዴ መሰረት በማድረግ ሚስጥሩ ቴአትርን በትኩረት በመመልከት፣ዕህፈተ ተዉኔቱን እና ስለ መድረክ ግንባታ የሚዳስሡ የተለያዩ መፅሃፎችን እና ድረገፆችን በጥልቀት በማንበብ እንዲሁም ቴአትሩ በሚሰራበት ወቅት የተሳተፉትን አባላት ቃለ መጠይቅ በማድረግ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ችሏል

1.6.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ሰንመለከት ከበዙ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር የሚነሱ የጥናቱ አሰራር ዘዴ በሚመች መልኩ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን ፤ በዋናነት ለጥናቱ የሚረዱትን ሶስት ዘዴ ተጠቅሟል እነሱም፦ ግላዊ ምልከታ ፣ ቃለ መጠይቅ ፣የሰነድ ትንተና ናቸው።

1.6.1.1 ግላዊ ምልከታ

አለም እሸቱ መሰረታዊ የምርምር እና የዘገባ አፃፃፍ(1984 ዓ.ም) በሚለው መጻፍ ምልከታ

ቅድሚያ ታቅዶ መሰረታዊ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሲባል የሚከናወን ትኩረትንና ምርምርን የሚዘግብ መረጃ ማሰባሰቢያ ስልት ነው። በማለት ገልጾታል። እጥኚውም ለጥናቱ ይረዳው ዘንድ የሚስጢሩ ቴአትር የመድረክ ግንባታን በቦታው ተገኝቶ በማየት የራሱን ምልከታን በመረጃ ተንትኖታል።

1.6.1.2 ቃለ መጠይቅ

ጠያቂና መላሽ ግንባር ለግንባር በማገናኘትና ጥያቄዎችን ለመላሹ በማቅረብ ከመላሹ መረጃ የሚትሰበስብበት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ነው። ይህም ሲባል ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን አካላት ቃለ መጠየቅ መደረግ ነው ። በምንጠይቃቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተሳታፊ፣ ተመልካች ወይም ከዝህ ቀደም ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ምርምር አድርጎ የሚያውቁ ከሆነና ጉዳዩን ለመግለጽ ፈቃደኛ ናቸው ብሎ ያመናቸው አካላትን አጥኚው ቃለ መጠይቅ ያደርጋል።

1.6.1.3 የሰነድ ትንተና

ተዕፎ የተቀመጠ፣ የታተመ አልያም ያልታተመ በዕሁፍ የተፃፉ እና ለመረጃ ተሰንዶ የተቀመጠ መረጃ መሰባሰቢያ ዘዴ ነው። አንድ አጥኚ የመረጃ መሰባሰቢያ መስሪያዎች የሰበሰባቸውን መረጃዎችን ተአማኒነት ለማረጋገጥ ያልተዳሰሱ ጉዳዮች አሉ ብሎ የሚያምን ከሆነ ልዩ የዕሁፍ መረጃዎችን ከተለያዩ ሰነዶች ላይ በመውሰድ የሰነድ ትንተና መተንተን ይገባዋል። ዳንኤል ዘውዴ(94፡1994) አጥኚውም ከዙህ ቀደም ለጥናታዊ ጽሁፍ የሚረዱ ወይም ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን መፅሀፎች የተለያዩ ጽሁፎች በማገላበጥ ለጥናቱ የሚረዱትን መረጃዎችን በመሰብሰብ ብሎም መተንተንን ተከትሏል ። ለምሳሌ ፦ አጥኚው ለጥናቱ ዕሁፉ የሚረዱትን ከመድረክ ግንባታ፣ ከኪነ- ህንፃና ከሚስጢሩ ቴአትር ጋር ተዛማጅ ያላቸውን መጽሀፎች ተጠቅሟል።

1.7 የጥናቱ አወቃቀር

አጥኚው በጥናታዊ ዕሁፉ ውስጥ አራት ምዕራፎችን አካቷል። በነዚህም ምዕራፎች ውስጥ የምንዳስሳቸው ነጥቦች ምዕራፍ አንድ የጥቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ ጥናቱ ዓላማ ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያዎች ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ መጠነ ርዕይ ፣የጥናቱ ዘዴ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠመቅ ችግሮች በምዕራፍ አንድ ውስጥ ተካቷል። በምዕራፍ ሁለት ላይተተኩሮ የሚሰራው የንድፈ ሃሳብ ቅኝተና የተዘማጅ ዕሁፎች የመቃኘት ስራ ሲሆን በዝህም ከጥናቱ ጋር በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን አጥኚው ፣ ኪነ-ህንጻ ማለት ምን ማለት ነዉ ፣የኪነ-ህንጻ ምንነት ፣የኪነ-ህንጻ ታሪካዊ ዳራ ፣ የቴአትር ምንነት ፣የመድረክ ግንባታ ታሪካዊ ዳራ ፣የቴአትር መድረክ አይነቶች ፣የቴአትር መድረክ ምንነት ፣የመድረክ ገጽ አላባዊያን ፣የመድረክ መሰረታዊ ትርጉም በምዕራፍ ሁለት ውስጥ አብራርቷል ምዕራፍ ሦስት ላይ ደግሞ ለጥናቱ የተሰበሰበ መረጃዎች መተንተን ይህም ሲባል። ምዕራፍ ሁለት ላይ ያገኘውን በመረጃ ተንተርሶ ጥናታዊ ዕሁፉን ተንትኖታል። ለምሳሌ፦ የመድረክ አይነቶች የመድክ ምንነት እና አመጣጡን ያስቀመጠውን በምዕራፍ ሦስት ከራሱ ሀሳብ ጋር በማነጻጸር ተንትኖታል። በመጨረሻም በምዕራፍ አራት ከመረጃ ትንተናው የተገኙ ግኝቶችን ዋቢ መፀሀፍትን ወይም የመረጃ ምንጮችን ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦችን መስጠትን በውስጡ ይይዛል።

1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው

አጥኚው ጥናቱን በምያስኬድበት ወቅት የመጀመርያው ችግር የነበረው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የመመረቂያ ፅሁፎችን ለማግኘት አስቸጋሪ ነበር። ይህ ችግር የመነጨው ጥናታዊ ፅሁፎች በአግባቡ ተሰንድው ባለመቀመጣቸው እና በብዛት አጥኚው ከሚያጠናው ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ተመሳሳይነት ያለውን ጥናታዊ ፅሁፍ ባለመኖሩ አጥኚው በብዙ ተቸግሯል ። በተጨማሪም በቂ የሆኑ መፀሀፎችን ለማግኘት ተቸግሯል ። ነገር ግን ባገኘው መረጃ መሰርት ጥናታዊ ፅሁፉን ለመስራት ችሏል ።

ምዕራፍ ሁለት

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

2.1.2 ኪነ-ህንፃ ማለት ምን ማለት ነው?

ኪነ–ህንጻ ማለት ጠንከር ያለ የሙዚቃ አገላለጽ ማለት ነው። ይህም ሲባል ሙዚቃ የውስጥ ደስታን ሊሰጥ የምችልና የሚያዝናና ነው። የ ኪነ–ህንጻ ጥበብ ደግሞ በአይን አይተን ከመደሰት ባለፈ የውስጥ አድናቆትን የሚያጭርልን ልዩ የሆነ የግንባታ ጥበብ ነው ። በመሆኑም የሰው ልጅ የዕለተለት ኑሮውን በሚኖርበት ወቅት በብዙ ነገር እራሱን ሊያስጨንቅ ፣ ሊያሳዝንና ሊያደክም ይችላል እናም የኪነ–ህንጻ ጥበብ ግንባታን ቢያይ ፡ ቢጎበኝ ምናልባትም ከድካሙና ከሃዘኑ ብሎም ከጭንቀቱ በነዚህ የጥበብ ግንባታ ቅርጽ እና ስዕል የዉስጡን ደስታ ይፈጥራል። ስለዚህ የኪነ–ህንጻ ጥበብ ጠንከር ያለ የሙዚቃ አገላለጽ ነው ለማለት አያዳግትም።

ኪነ–ህንፃ ማለት የስነ–ጥበብ ሳይንስ እና የግንባታ ማቋቋሚያ ጥበብ ማለት ነው። ጀአሜሊን ኦሮን. ኤለመንትስ ኦፍ አርክቴክቸር ሂስቶረ በሚለው መጸሀፍ ላይ እንዲ ሲል አስቀምጧል። "ኪነ–ህንፃ የሚለው ቃል ከግሪክ የመጣ ቃል ሲሆን ይህም አርክቴክቶን ይሚለውን ሂደት ነው። ትርጓሜውም ህንፃ መሰረት (የህንፃ ስራ ወይም አሰራሪ ስብስ) ማለት ነው። ሌላው ኪነ–ህንጻ ማለት ጠንከር ያለ ግንባታ ሂደት ማለት ነው። (ጀአሜሊን ኦሮን21፥ 1975)(3)"

2·1·2 የኪነ-ህንፃ ታሪካዊ ዳራ

አራያ.ጂ. ዋቁማ.ቲ ሂስቶሪ ኦፍ ኢትዮጵያን አርክቴክቸር· በሚለው በፀሀፍቸው ላይ "ኪነ-ህንጻ የጀመረው በ400B·C ነው ። በወቅቱ አደን በሚታደንበት ለአደን የሚሆናቸውን መሳርያ ቀረጹ ቀጥሎም ለምግብነት የሚያገለግላቸውን ሸክላ ሰሩ"። (65፥ 1975) (2) ብለው አስቀምጠዋል በተጨማሪም በዚሁ መጸሀፋቸው ላይ እንዲህ አስቀምጠዋል። የኪነ-ህንፃ ጥበብ የጀመረው በግብፅ ነው። በ2635-2995 B·C ከዚህ ግዜ ጀምሮ የኪነ-ህንጻ ግንባታ መጣ። ይህም የመጀመርያው የፒራሚድ ግንባታ ነው። በወቅቱ ከተለያዩ ቦታ የመጡ የኪን-ህንጻ ጥበብ የመገንባት ሙያ ያላቸው ሰዎች እና ሌሎችም የተለያዩ ድንጋዮችን በመጥረብ ለመጀመሪያ ግዘ የፒራሚድ ግንብ በግብፅ ገነቡ። (አራያ.ጂ .ዋቁማ.ቲ 7፥1975) ሌላው እንደ ሀገራችን ስንመለከት ደግሞ የመጀመርያው ግንባታ የጀመረው ፕሪ— አክሱማይት, ሳቤን ኤራ,አክሱማይት አርክቴክቸር, ጎንደሪያን አክቴክቸር, አዲስ አበባን አርክቴክቸር እያለ ነው አሁን ያለንበት ደረጃ የደረሰው በማለት ዶር.ላቢሶ ግ.ዩሌቦ.ሂስቶሪ ኦፍ ኢትዮጵያን አርክቴክቸር በሚለው መጸሀፉ አስቀምጠውታል (ዶር.ላቢሶ ግ.ዩሌቦ8፥1987)

2·1·3 የቴአትር ምንነት

ቴአትር በተዋንያን አንደበት ተቀነባብሮ በውይይት ወይም በግል መነባነብ ተዘጋጅቶ በአካል ንቅናቄ ተደግፎ በስነ-ጽሁፍ ድርሰት ላይ ተመስርቶ በውብ ንግግር እና በሰውነት እንቅስቃሴ ቀርቦ በመድርክ ላይ ተተውኖ የተመልካችን አይን ከመማረኩ የተነሳ ተሳክቶ የሚታይ ድራማዊ ድርግያ ያለው ኪነ-ጥበብ ነው። ዘሪሁን አስፋው የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን በሚለው መጸሀፉ ላይ " ቴአትር ገና ከመነሻው በተዋንያን አማካኝነት መድረክ ላይ የሚቀርብ በመሆኑ ከሌሎች በአያሌው የተለየ ነው። (ዘሪሁን አስፋሁ ፣ 16 ፣ 1992) በማለት ስለ ቴአትር ገልጾአል። በተጨማሪም ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዘገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ በሚለው መጻፉ ላይ እንደሚከተለው አስቀምጧዋል። ቴአትር ፣ ቲአትር እና ቴአትር በሚሉ ተለዋዋጭ መጠርያ

ይጠራል፡፡ የተውኔት ወይም የድራማ ኪነ-ጥበብ አጠቃላይ ገጠመኝ ነው፡፡ ቲያትር የሚለው ቃል በአጠቃላይ ቤተ ተውኔቱን ወይም ህንጻውን ፣የአገልግሎት ሰጪ ቢሮዎችን የተውኔት ድርሰት ፣ የተውኔትን ሙያ ፣ የተውኔት ንቅናቂ እና አቀራረብ ስልት እንዲሁም የጥቅል አገልግሎት መጠርያ ነው፡፡ (ፋንታሁን እግዳ 18 ፣ 1993)

2.1.5 የመድረክ ምንነት

መድረክ ተዋንያን፣ ሙዚቀኞች፣ ተወዛዋዞች ዝግጅቶቻቸውን ለተመልካች የሚያቀርቡበት እና የሚከውኑበት ቦታ ወይም ስፍራ ነው፡፡ መድረክ የቤት ዉስጥ እና የቤት ዉጭ ስፍራን ይወክላል፡፡ ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸውን ከ ሀ ውስከ ፐ በሚለው መጻፉ ላይ እንዲህ ገልጾታል፡፡ "መድረክ በተለያየ መጠን ፣ ቅርጽ እና አይነት ይዘጋጃል፡፡ መድረክ ጥራት የሌለው ነው ከተባለ የታቀደው ትርዒት በአቧራማ ስፍራ፣ በገብያ ቦታ፣ በጭነት መኪና ጀርባ ላይና በአጠቃላይ በገላጣ ስፍራ ሊቀርብ ይችላል፡፡" (ፋንታሁን እንግዳ ፣ 27 ፣ 1993) ሌላው መድረክ ማንኛውንም የጥበብ ስራ የምናይበትና የምንከውንበት ቦታ ነው ፡፡ ይህም ሲባል ተመልካች ቁጭ ብሎ ወይም ቆሞ ተዋንያኑን የሚይበትና ተዋንያኑም የራሳቸውን ስራ የሚሰሩበትና የሚከውኑበት ቦታ ነው፡፡

ቴአትር ብዙ ተለዋዋጭ ስያሜ እንዳለው እና ስለ ቴአትር አጠቃልይ ምን እደሚመስል ከላይ ባለው ዝርዝር መረጃ መሰረት ፋንታሁን እንግዳ ገልጾታል፡፡ ይህም ቴአትር ብዙ መጠርያ እንዳለውና ብዙ ጥልቅ የጥበብ ክፍል እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

2.1.6 የመድረክ ግንባታ ታሪካዊ ዳራ

ሂስቶሪ ኦፍ አርክቴክቸር ስቴጂ ቴአትር ቴክኖሎጂ በሚለው መጻሀፍ ላይ ጃኔ, ስክሬበሪ ስለ ቴአትር መድረክ መገንባት እንዲህ ገልጾአል፡፡ የቴአትር መድረክ ወይንም መተወኛ ስፍራ የተጀመረው በግርክ ከተማ ነው፡፡ በወቅቱ የመድረክ መገንባት ምክንያት የሆነው የሀይማኖት ቤተ መቅደስ ነበር፡፡ ከዛ ጋር ተያይዞ ቴአትር በተለያየ ቦታ ቢቀርብም ከ 1500 B.C ጀምሮ የአምልኮት ቦታን (ቤተ መቅደስ) ቅርጽ የሚመስል ወይንም ከአምልኮ ቦታ ጋር ተያያዥነት አለው ተብሎ

ስለሚታሰብ በክብ መድረክ በግሪክ በ 1500 B·C መተወን ተጀመረ። (ጃኔ ,ስክሬበሪ፣ 29 ፣ 1985)(5)

ለመጀመሪያ ግዜ የመድረክ ግንባታን ንድፍ ያወጣው ኢ,ኒጎ ጆሆን በ 1573–1652 የቴአትርን መድረክ ንድፍ አደረገ ። የቴአትር መድረክ እንደ ሀገራችን ማለትም እንደ ኢትዮጵያ በ 1948 ፣ በ ቀዳማዊ ሀ / ስላሴ ህዳር 3 ተጀመረ ። ተብሎ ይነገራል የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር አጭር ታሪክ እና የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚለው መጻፋቸው ፍቃዱ ፋየ እና እቴነሽ ካሳ ገልጾታል ። (40 ፣ 2000)


2·1·7 የመድረክ አይነቶች

ስለ መድረክ አይነቶች ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ በሙለው መጸሀፉ ላይ እዲህ ሲል አስቀምጧል ። " ዘመናዊ የመድረክ አይነቶችና የ መጠርያ ስሞች ከ ተመልካች ጋር ባላቸው የቅርበትና የርቀት ግንኙነት ላይ ተመስርተው የተሰጡ ናቸው ። ዘመናዊ የሆኑትና እንዲሁም አልባሌ የመድረክ አይነቶችን ጨምሮ የፊትለፊት ፣ ሶስት ጎን ፣ ክብና አካባቢዊ የመድረክ አይነቶች ተብለው በአራት ይከፈላሉ (ፋንታሁን እንግዳ ፣ 18 ፣ 1993)

ፋንታሁን እንግዳ ከላይ እንደገለጸው የመድረክ አይነቶችን በአራት መንገድ ይከፍላቸዋል ። እነሱም የፊት ለፊት ፣ ሶስት ጎን ፣ ክብና አከባቢዊ ምድረክ በማለት ያብራራቸዋል

2·1·7·1 የፊትለፊት መድረክ

የፊትለፊት መድረክ ከተመልካች ፊትለፊት ትርኢት የሚቀርብበት የመድረክ አይነት ሲሆን ከተውኔት ታዳሚው መቀመጫ ፊትለፊት ከፍ ብሎ የሚገነባ የመተወኛ ቦታ ነው ። ፋንታውን እንግዳ የተውኔት አላባውያን በሚለው መጸሃፉ ላይ እንዲህ አስቀምጧል ። "የፊትለፊት መድርክ ከባለ ክብ መድርክ እና ከባለ ሶስት ጎን መድርክ የበለጠ እውነታዊ ነው ። ከነዚም የተነሳ ይመስላል ብዙ መጸሃፈ ተውኔቶች ተውኔቶቻቸውን ለዚህ እውነታዊ ለሆነው የፊትለፊት መድረክ አዲስ ማማ አድርገው የሚጽፉት ። (ፋንታውን እንግዳ ፣ 187 ፣1992)




በተጨማሪም ፋንታሁን እንግዳ በሌላኛው መጸሃፉ ተውኔታዊ መዝገብ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ በሚለው መጸሃፉ ላይ በስል አስቀምጧል ። የፊትለፊት መድረክ እንዳይኖር እንቅፋት ከመሆኑም በላይ ተዋንያን ካለ አገባብ ለተመልካች ገዘፈው እንዲታዩ ምክንያት ነው ተብሎ ይታመናል ።(ፋንታውን እንግዳ ፣ 41 ፣ 1993) በማለት አስቀምጧል ። በተጨማሪም የፊት ለፊት መድረክ አመቺና አስተማማይ ከመሆኑ የተነሳ በተመልካችና በተዋንያኑ ዘንድ ተመራጭ ነው።

2.1.7.2 ባለ ሶስት ጎን መድረክ

ሶስት ጎን መድረክ የምንለው በቅርጹ ከፊት ለፊት መድርክ እና በክብ መድረክ መካከል የሚገኝ ነው። ለምሳሌ፡ባለ ሶስት ጎን መድረክ በአቀማመጡ ከክብ መድረክ ጋር ይመሳሰላል። ሲገነባም ዙርያው ጥምጥም መልክ ይዞ ነው። ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገብ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ በምለው መጸሀፉ ላይ "ሶስት ጎን መድረክ አቀማመጥ በአብዛኛው እንደ ክብ መድረክ ሁሉ ከተመልካች መቀመጫ ዝቅ ብሎ የሚገነባ ነው። "(ፋንታሁን እንግዳ ፣ 42 ፣ 1993) በማለት አስቀምጧል። በተጨማሪም የተውኔት አላባውያን በሚለው መጻሀፉ እንዲህ ይገልጻል። "የሶስት ጎን መድረክ አቀማመጥ አልፎአልፎ እንደ ፊት ለፊት መድረክ ከተመልካች መቀመጫ ከፍ ብሎ የሚሰራበት ግዜም አለ። እንደ መድረኩ መግዘፍና ማነስ ወድያ

በተመልካችና በተውንያን ዘንድ በስነ-ልቦና በአካል መቀራረብ የመነጣጠል ስሜትይፈጥራል። (ፋንታሁን እንግዳ ፣ 214 ፣ 1992)




እናም የባለ ሶስት ጎን መድረክ ተጨማሪ ጠቀሜታ ያለው በተመልካችና በተዋንያን መካከል ቅርርብ እንዲፈጠር ከመርዳቱም ባለፈ ተዋንያኑ በሚተውኑበት ወቅት ከትይንት ወደ ትእይት እንዲሁም ከአንዱ ገቢር ወደ ሌላ ገቢር ለሚደረገው ሽግግር አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር ስለሚችል ነው ። በመሆኑም የባለ ሶስት ጎን መድረክ ለተዋንያኑም ፣ ለተመልካችም አመቺ ስለ ሆነ በብዛት ይመረጣል ።

2.1.7.3 ክብ መድረክ

ክብ መድረክ የምንለው በተመልካች ዙርያውን የተከበበ የመተወኛ ስፍራ ነው ። ክብ መድረክ ከሌሎች የመድረክ አይነቶች ማለትም ከፊት ለፊት መድረክ የሚለይበት አንዱ መንገድ የመድርኩ አቀማመጥ መቃረን ነው ። ምክንያቱም ክብ መድረክ ሲገነባ ከተመልካች መሀል ገቸ ብሎ ነው። Edwin Wilson the theatre experience በምለው መጻፍ ላይ ፦ "ክብ መድረክ ከፊትለፊት

መድረክ የሚለይበት ሌላዉ ነጥብ የዳራዊ ቅብ አለመጠቀሙ ነው ። በዚህ የተነሳ በክብ መድረክ ስራ ላይ አይውልም ።" (Edwin Wilson , 56 ,1976) (6) በማለት ገልጾአል ።



ክብ መድረክ የምንለው ከልዩልዩ ስርአት አምልኮ ማክበሪያ ጋር እና ስፍራዎች ሳይወረስ እንዳልቀረ የሚያስረዱ ብዙዎች ናቸው ። በተለይ ደግሞ ከጥንት የግሪክ ሀይማኖት ክብረ በአላት መከወኛ ቦታና ማወደሻ ስፍራዎች ጋር ተመሳስሎ እንዳለው አይነተኛ ማስረጃ ሆኖ የሚቀርብበት አጋጣሚ እና ሁኔታ አለ ድንገት ነው ተብሎም ይታሰባል ።

2.1.7.4 አካባቢያዊ መድረክ

አካባቢያዊ መድረክ የምንለው ከላይ የተገለጹት ማለትም ከፊት ለፊት መድረክ ከክብና ፣ ከሶስት ጎን መድረክ የአንዱን ወይም የሁለቱን አልያም የሶስቱን መድረኮች የሚለይበት መንገድ በትኛውም ገላጣ ስፍራ መስራት ስለሚቻል ነው ። ለምሳሌ በገብያ ፣ በትምህርት ቤት ፣ አዳራሽ ፣ ምንገድ ዳር እና በአልባሌና መድረክ የሌለው አዳራሾች መቅረቡ ነው ። ። ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገብ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ በሚለው መጸሃፉ ላይ እንዲህ አስቀምጧል ።

"የአካባቢያዊ መድረክ የትወና ስፍራዎች ያን ያህል እንደ ሶስቱ ደንበኛ መድረኮች የተገደበ በማለትም የተወሰነ አይደለም ። ስለ ሆነም አስፈላግ በሆነበት ግዜ ሁሉ በአካባቢያዊ መድረክ ትርኢት የሚያቀርቡ ተዋንያን ከታሰበው የበለጠ የትወና ስፍራ

2.1.8 የመድረክ መሰረታዊ ትርጉሞች

ቀኝ መድረክ ፦ ፊቱን ለተመልካች ሰጥቶ መድረክ ላይ የቆመው ተዋናይ ቀኝ። ግራ መድረክ ፦ ፊቱን ለተመልካች ሰጥቶ መድረክ ላይ የቆመው ተዋናይ ግራው ። ታችኛው መድረክ፦ ለተመልካች የሚቀርበው የመድረክ ክፍል ። ላይኛው መድረክ ፦ ከተመልካች የሚቀርበው የመድረክ ክፍል ። ውስጥ ፦ በመድረኩ መሀል አካባቢ ። ውጪ ፦ ከመድረኩ መሀል የራቀ

2.1.9 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

አጥኚው ከዚህ ቀደም ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጥናታዊ ስራዎችን ባያገኝም ከዚህ ቀደም የተሰሩና ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች የተመለከተ ሲሆን በ1980 ዓ.ም የሻሸወርቅ በየነ አዲስ አበባ " የቤተ-ቲያትር ኪነ-ህንጻ በሀገር ፍቅር ቲአያትር ማስረጃነት " በሚል ርዕስ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዖፍ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን በውስጡም ሁለት ምዕራፎችን ይዟል ። በመጀመርያው ምዕራፍ ቤተ ቲያትር ከየት ወዴት የሚል ሲሆን ፡ ሁለተኛው ምዕራፍ ድግሞ ስለ ኪነ-ህንጻ የጥበብ ጥልቀት የተሻለ ያስረዱ ቤተ ቴአትሮች እንጂ እንደ መካከለኛው ዘመን የነበሩበት ተንቀሳቃሽ መድረኮች አይጨምርም የሚል ነው ። ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከዚህ ጥናት ጋር አንድ ሚያደርገው ስለ ኪነ-ህንጻ ምንነት እና ስለ ቴአትር መድረክ ግንባታ ማንሳቱ ነው ። የምለየው ደግሞ ጥናቱ በሁለት ምዕራፍ መከፈሉ ፣ በአንድ ቴአትር ቤት መወሰኑ ሲሆን አጥኚው ደግሞ በቴአትር አስረጅነት የኪነ-ህንጻን ጥበብ መስራቱ ከጥናታዊ ፅሁፉ ይለያል ። ሌላኛው በ 1988 ዓ.ም ቢያደርገው መልካሙ ኪነ-ህንጻ ከሀገር ፍቅር መድረክ አኩዋያ በምል ርዕስ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዖፍ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው ። ይህ ጽሁፍ ከዚህ

ጥናት ጋር አንድ የሚያደርገው ስለ ኪነ-ህንጻና ስለ ቴአትር አስረጅነት ስለ መድረክ ታወራለች ።

ጥናቱ ደግሞ ስል አንድ ቴአትር መድረክና ውጫዊ ውበቱ የሚያወራ ነው ። በመሆኑም ከአጥኚዋ ጋር በዚህ መልኩ ይለያል ።

ምዕራፍ ሶስት

3.1 የመረጃ ትንተና

3.1.1 የሚስጥሩ ቴአትር ጭምቅ ታሪክ

ትዕይንቱ የሚጀምው ከዋዘሮ ብርቁ ቤት ደጃፍ ላይ የሰፈሩ ወጣቶች አራቁ እየጠጡ በግራ አና ቀኝ ተደርድሮ ተቀምጠዋል ። አዝማሪዉ ቻሌ አና ሚስጥሩ ከተቀመጡ ወጣቶች ፊትለፊት ቆመዉ አዝማሪዉ ማሲንቆዉን እየገዘገዘ ሚስጥሩ ግጥም እየሰጠዉ የተቀመጡት ሁለቱ የሚስጥሩ ጓደኞች ያጨበጭባሉ ሚስጥሩ የጎጃምን እስክስታ እየመታ ያስተርተዋል። በጎን የተቀመጡት ሶስት ወጣቶች አንገታቸዉን ደፈተዉ በንዴት ተቀምጠወ ይጠጣሉ።

የነሱ ጓደኞች አይቼና ሞቼ ይተባሉ አይቼ ከሚስጥሩ ጋር በፊት በሴት ጠብ ስለነበረዉ ሚስጥሩን ሲያየው ተምልሶ ሊወጠ ሲል አብሮት የመጣዉ ሞቼ እንዳይወጣ ይይዘዋል አይቼም ተመልሶ መዉጣት ይፈልጋል ።ሞቼ ደግሞ እሱ እንደፈለገ እየተዝናና አነተ ለምን ትወጣለህ በማለት ። መምታት ካለብህም ቦታዉ ያመቻል ብሎ አበረታቶ ያስቀምጠዋል ። ከዝያም የተቀመጡት ሶስቱ ጓደኛሞች ጎን ይመለከታሉ አዝማሪዉም ከሚስጢሩ ጋር ይጫወታል አይቼና ሞቼም አዝማሪዉን እንዲያጫዉታቸዉ ይጠሩታል ።

አዝማሪውም ሚስጥሩ ከጎኑ ስለቆመ ወደ ሚስጥሩ ዞሮ መሲንቆዉን እየመታ ይጫወታል ። አይቼና ሞቼ በንዴት በድጋሚ እኛንም አጫዉተን እንጅ ንቀት ነዉ እንዴ ይሉታል አሁንም ወደ ሚስጥሩ ዙሮ ይጫወታ አይቼም በንዴት አታጫዉተንም እንዴ ሲነሳበት ወደ እሱ ዙሮ ይጫወታል ። ሚስጥሩ ሁለቱ ጓደኞቹ ጋር ሄዶ ይቀመጣል ። አዝማሪዉ " ሆይ መላ ነሻ አሉ ሆይ መላ " ብሎ ሲጫወት አይቼ የምን መላ መላ ነዉ የምትለዉ የወንዶቹን ዘፈን " አያ በለዉ በለዉ " ብለህ ተጫወት ይለዋል ። አዝማሪውም " አያ በለዉ በለዉ " በማልት ይጫወታል " አያ በለዉ በለዉ ማልት ና ግጠመኝ እንደማልት ሲሆን ሚስጥሩ ተንኮል እንዳሰበ ይገበዋል እነ አይቼ ቁጭ ብሎ አረቂያቸውን እየጠጡ ፣ እስክስታ እየመቱ አብሮ ይዝናናሉ።

ከዝያም የሚስጥሩ ወንድም አያሌዉና ፈሪዉ ጓደኛዉ ጣፈጠ ይገባሉ አያ በለዉ በለዉ የሚለዉ ዘፈን ሲሰሙ ጣፈጠም ፈርቶ የምን ጠብ ነዉ አያሌዉን ይጠይቀዋል ዝም ይለዋል ፤ ጣፈጠም እኔ ጠብ አልወድም እንሂድ ይለዋል። የሚስጥሩ ወንድም አያሌው ከ ወንድሙ ጋር ስለማይዋደድ እነ


አይቼን ሰላም ብሎ ይቀመጣል ጣፈጠም የሚስጥሩን ንዴት አይቶ እሩጦ ይወጣል ። አዝማሪዉም እነ አይቼን ማጫወት ይጀምራል ከዝያም አንዱ ተንስቶ " ዲንጋይ ተንከባሎ ሲያገኝ መደላደል ፣ ወተት ይሸፈታል እንኳን ሰዉ ሲበድል " ብሎ ሲተርት ይስቃሉ ሚስጥሩ እየሳቀ ያስተርታል " ወተቱ ቢሸፈት ተገፍቶ ተገፍቶ ቅቤ ይወጣዋል በገዛ እጁ ለፍቶ " ጓደኞቹ ይስቃሉ እነዚያኞቹም ተንስቶ በሚስቱ ያስተርቱበታል ከዚያም ተራ በተራ ይተራረባሉ ። ብዙ ከተተራረቡ በሁኋላ ሁለቱ በጣም ይናደዳሉ ሊጣሉ ይሉና እርስ በእርስ ይገላገላሉ ።

በድጋሚ መተራርብ ይጀምራሉ በፊት በሴት የተጣሉት ሚስጥሩና አይቼ በአዝማሪዉ ግራና ቀኝ ቁመዉ አዝማሪዉን በል ይሉታል አዝማሪውም የማንኛቸዉን መቀበል እንዳለበት ግራ ገብቶት እያለ፤ በመሀል ይጣላሉ ። አያሌዉም መሀል ገብቶ ይገላግላል ሁለቱም ይፎክራሉ አይቼና ሞቼም እየተናደዱ ተያይዘዉ ይወጣሉ ። ሚስጢሩም ቁሞ ወይኔ እያለ ይናደዳል አዝማሪውም የንዴት የማሲንቆ ድምፅ ይገዘግዛል ሚስጥሩም የ አይቼን ጓደኞች እየሰደበ ተራ በተራ ያስወጣቸዋል ። ከዚያም የሰፈሩ ባል ጸጋ አያ በላይ በፈጥነት ገብተዉ ልጁ እንደታመመችበት ያበደረዉን ብር በአፋጣኝ እንዲመልስለት ይጠይቀዋል ሚስጢሩም ለምስጠት ፍቃደኛ አይደለም አያ በላይም ተንበርክኮ ይለምነዋል ሚስጥሩም አሻፈረኝ አልሰጥም ይላል አያ በላይም ልጄ ከሞተች ግን አንተና እኔ አንዛለቅም እያለ እየተናደዱ ይወጣሉ ። በቀጣይ ገቢር ትዕይንቱ ሲጀምር ሚስጥሩ ሙቶ የአከባቢው ህብረተሰብ ከ ዳኝነት ቦታ እንዲገኙ በጡሩንባ ለፋፊዉ ይናገራል በዚያም መሰረት አከባቢው ከሚዳኝበት ዋርካ ስር ወጣቶች ፣ እናቶች ፣ አባቶች ፣ ሽማግሌዎች ፣ ቄሶች ፣ መሪ ጌታ ፣ ጸሀፊ ትዕዛዛት እና መሳርያ ያላቸዉ ጥበቃዎች በሙሉ ይገኛሉ ። ከዚያም በኋላ ወደ ዳኝንት ስነ ስረዓት ይገባሉ ። ተጠርጣሪ ሰዎችን በማጋልጥ የተጠረጠረዉን ሰዉ በመጠየቅ ገዳዩ እንዲታወቅ ያጣራሉ ከዚያም በማጣራት ሂደት ዉስጥ ትክክለኛዉን ሰዉ ባለማግኘታቸዉ በድሮ በአባቶቻችን የአፈራረድ ስነ ስረዓት ሁለት ጥይት የተቀባበለ መሳሪያ በማጋደም ወደ ፍርዱ ሂደት ይገባሉ ። " ይህኛው ቢስተኝ ያኛው አይሳተኝ" እያሉ እንዲዘሉ ያሟቸዋል ።

3.1 .2 የሚስጢሩ ቴአትር የመድርክ ግንባታ

የሚስጢሩ ቴአትር መታየት ከጀመረበት ዕለት አንስቶ ማለትም 2011 ዓ.ም ጀምሮ አሁን እስካለንበት ድረስ ከ ቀን መለወጥ በስተቀር በቤሄራዊ ቴአትር እየቀረበ ይገኛል ። ይህ ተዉኔት በጎጃም መህበረሰብ አጥፊዉን የሚያወጣጡበት አዉጫጪኝ የሚባል የዳኝንት ስረዓት ነዉ ። በህልና ልማድ የሚያሳይ የሙሉ ግዜ ተዉኔት ነዉ ። የሚስጥሩ ቴአትር የምድርክ ግንባታ

ዕሳቤው መቼቱን እና ዘዉጉን በደምብ ገልጾታል። እንደ ሀገራችን እየተጠቀምን ባለው የመድርክ አገነባብ የተገባ ነው ። ነገር ግን ከአንዱ ትዕይንት ወደ ሌላ ትዕይንት ሲሸጋገር ደግሞ በ senery የታገዘ ነው ። የ ሚስጢሩ ቴአትር የመድርክ አይነት የፊትለፊት የምንለዉን የምድርክ አይነት ነው ። በመሆኑም የሚስጥሩ ቴአትር የመድርክ ግንባታ ይህን ይመስላል ።



የፊትለፊት መድርክ ስዕል

የፊትለፊት ምድርክ አገንባብ ሁሉን ያማከለ ለተመልካች ምቹ የሆነና ለተዋንያኑም ጥሩ መተወን እንዲችሉ የሚያግዝ ነው ። በመሆኑም የሚስጥሩ ቴአትር በዝህ አይነቱ የመድርክ ግንባታ ይቀርባል ። እንደ አጥኚው አመለካከት የሚስጥሩ ቴአትር ታሪክ የመድርክ ግንባታ ለ ፕሮሲኒዬም እስቴጅ ቢሆን ምቹ ነው ብሎ ያምናል ። ምክንያቱም ካሉት ዬምድረክ አይነቶች መሀል ፕሮሲንዬም እስቴጅ የምንለው የምድረክ አይነት ለተመልካቹም ፣ ለተዋንያኑ ፣ ለአዘጋጆቹም ምቹ እንደሚሆነ አጥኚው ከዚህ ቀደም በተማረው ትምህርትና ባገኘው መረጃ መሰረት አመቺ መሆኑን ተገንዝቧል ። እናም የሚስጢሩ ቴአትር የመድርክ ግንባታ በፊትለፊት መድረክ መሆኑን አጥኚው ይደግፈዋል ። ለምን ቢባለ እንደ ሀገራችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ብንመለከት እንኳን ብዙ ወጪ የማያስወጣን ፣ ለአልባሳት ፣ ለገፀ ቅብ ፣ ለመተወን ምቹ ነው ብለው ስለሚያምን ነው ። ስለዝህ ተመልካቹ ከፊትለፊት ሁኖ ተዋንያኑ ለተመልካች ጀርባ ሳይሰጥ ፣ አልባሳት ለመቀየርም ፣ ገፀ ቅብ ለመሰራትም ሳይቸገሩ በተሳካ ሁኔታ እንዲተውኑ ስለሚያግዛቸው ተዋንያኒም ታሪኩን እንዲረዱና እንዳይጉላሉ ስለሚረዳቸው ነው ።

በተጨማሪም በፊትልፊት መድረክ ህግ መሰረት ተዋንያኑ አራተኛ ግድግዳን በመጣስ እንደታሪኩ መሰረት መተወን ይችላል ። እናም የሚስጥሩ ቴአትር ይህንኑ ተግባር ሲያደርግ ይታያል ። ለምሳሌ በተመልካች መሀል እየዞሩ እንዲተውኑ እና ተዋንያኑ እንደልባቸው እየተንቀሳቀሱ የተመልካችን ስሜት እንድይዙ ለማድረግ የፊትለፊት መድረክ መሆኑ አግዟቸዋል ። ስለዝህ አጥኚው ከዝሁ ነገር በመነሳት የሚስጥሩ ቴአትር የመድርክ ግንባታ በፊትልፊት መድረክ መሆኑን ምቹ ነው ይላል ። የፊትለፊት መድረክ አገንባብ ሁሉን ያማከለ ለተመልካች ምቹ የሆነና ለተዋንያኑም ጥሩ መተወን እንዲችሉ የሚያግዝ ነው ። በመሆኑም የሚስጢሩ ቴአትር በዝህ አይነቱ የምድረክ ግንባታ የቀርባል

3.1.3 የሚስጥሩ ቴአትር የምድረክ ግንባታ አጠቃላይ ዳሰሳ

የሚስጢሩን ቴአትር የምድረክ ግንባታውን አጠቃላይ ስንመለከት ማለትም ከትዕይንት አንድ እስከ መጨረሻው ገቢር ሁለት ትዕይንት አንድ ድረስ ያለውን የምድረክ ግንባታውን አጠቃላይ ዳሰሳውንና ለመድረክ ግንባታ የተጠቀሙትን ቁሳቁስ ፣ ሲናሪ ስንት እንደ ሆነ አጥኚው በአሰባሰበው መረጃ መሰረት ተንትኖታል ። ለምሳሌ፦ ብንመለከት ገና ትዕይንቱ ሲጀሚር የመድርኩ ግራ ጎን የጎጆ ቤትና ያለቅጥ የርዘመ በስተቀኝ በኩለ የኮባ ቅጠል እና አረቄ ቁጭ ብሎ ሚጠጡበት መደብና ኩርሲ አለ ይህም ደግሞ የመድረኩን ሁኔታና የታሪኩን መቼት የሚገልጸልን ነው ። በገቢር አንድ ትዕይንት አንድ ሚስጥሩና ጓደኞቹ ፣ የሰፈሩ ወጣቶች ማታ የብርቁ አረቄ ቤት ውስጥ ነው ። እናም የቴአትሩ መድረክ ሲገነባ ሲናሪውም የተለየ መድረክ ማድመቅያና ከታሪኩ ጋር የሚመሳሰል ዘመኑን (ግዜውን) የሚወክል ሁኖ ነገር ግን በአንዳንድ ችግር ምክንያት የመድርክ ግንባታው አለምሚላቱ የሚስተዋልበት አጋጣሚ አላ

። በመድረክ ግንባታ ያሉት እያንዳንዳቸው ነገሮች የራሳቸው የሆኑ ፊቺና ተምሳሌታዊ የሆኑ ተግባር አላቸው ። ለምሳሌ ፦ በሚስጥሩ ቴአትር ላይ ተዋንያኑ የሚለብሱ አልባሳት ከአከባቢው ጋር ተዛማጅንት እንዳለው አጥኚው ለማስተዋል ችሏል ።ሁለተኛው ምሳሌ ብመድርኩ ያሉት ቁሳቁሶች ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ግዜውንና ዘመኑን ያመላክተናል ። ሌላኛው ደግሞ ግበዓት ብርሃን ነው (ማብራት ነው) ። በሚስጥሩ ቴአትር ትዕይንቱ ሲቀየር ያሉትን መቼት የሚገልፅልንና የሚጠቁመን ግበዓት ብርሃን ነው ። ለምሳሌ፦ የመምሸት ፣ የድስታ ፣ የፍርሃትን ፣ አንዱ ከአንዱ ጋር ያለዉን ልዩነት እና እያንዳንዱን ነገር የሚገልፅልን ግበዓት ብርሃን ነው ። በአጠቃላይ ከላይ

የተገለፀትን እያንዳንዱ ሂደት በአጥኚው አመለካከትም አዎ ይገልፃሉ የሚል እምንት አለው ። ምክንያቱ አንድ ቴአትር ለመስራት ከታሰበና መድርክ ለምገንባት ከተፈለገ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች በሙሉ ያስፈልጉናል ። ለምሳሌ፦ የመድርክ ቁሳቁስ ፣ ፣ አልባሳት ፣ ግበዓት ብርሃን ፣ ግበዓት ድምፅ ፣ እና ሌሎች ነገሮችም የቴአትሩ አንድ አካል ሲሆኑ ለመድርክ ግንባታ ደግሞ ውበትና ምሶሶ ነው ለማለት ያስችላል ። ስለዝህ አጥኚውም የዘመኑን ወይንም የድባቡን ሂደት ከአንዳንዱ ችግር በስተቀር ይገልጻሉ ብሎ ያምናል ። እናም አንድ የቴአትር ታሪክ ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች በሙሉ ካሟላና ከታሪኩ (ከዘመኑ) ጋር ከተዋሃደ አንድም የዛን ዘምን ያለውን ታሪክ ይገልጻል ፤ ሌላው ደግሞ የመድርኩን ግንባታ ውበት ይገልፃል ። በመጨረሻም የሚስጥሩ ቴአትር ግንባታው አጠቃላይ ዳሰሳዉን ስንመለከት ከታሪኩ ጋር አብሮ የሚሄና ለማመሳሰል የትጣረው ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በዛን ዘምን ያሉትን አይነት ኩርሲ ፣ የአረቄ መጠጫ ፣ መሳርያዎች ተጠቅመዋል ። እናም ከአጠቃላይ ዳሰሳው ላይ በምንሳት የሚስጥሩ ቴአትር የመድርክ ግንባታ ደካማና ጥሩ ጎኑን በማንሳት በሁለት መንገድ ዳስሶታል ።

3.1.4 የሚስጥሩ ቴአትር መድረክ ግንባታ ደካማ ጎን

አጥኚዉ የሚስጢሩን ቴአትር ከመድርክ ግንባታ ዕሳቤ አንፃር ያልበትን ደካማ ጎኑን በዝርዝር አይቶታል በአገኘው መረጃ መሰረት ከራሱ ሀሳብ ጋር አንድ ላይ ያብራራዋል። ትዕይንቱ ገና ሲጀምር በአማራ ክልል ጎጃም የምትገኝ ትንሽዬ የገጠር መንደር ውስጥ ይጀምራል ። የቴአትሩ ታሪኩ በሚጀምርበት ዘመን የንበሪው ቁሳቁስ እና አሁን ቴአትሩ በንበረበር ወቅት ያሉት ቁሳቁስ ልዩነታቸዉ ምንድነዉ ስንል ፦ አሁን እኛ በመድረክ ላይ የተጠቀምናቸዉ ቁሳቁሶች በዛ ግዜ የነበሩትን አስመስለን ነው እንጅ ሁሉም በወቅቱ የንበሩ አልነበሩም ። ሁኖም አንዳንድ ችግሮች አሉ ለሚሳሌ ቁሳቁስን ብንመልከተው አረቄ የሚቀዳበት እና የሚጠጣብት አሁንላይ ያለዉን የመጠጥ ጣርሙስ የተወሰነ ተጠቅመዋል እሱ አንዱ ድክመት ነው ብሎ ያስቀምጣል አጥኚው

3.1.5 የሚስጥሩ ቴአትር መድርክ ግንባታ ጥሩ ጎን

የሚስጥሩ ቴአትር መድርክ ግንባታ ጥሩ ጎኑ እንብዛም ቢሆንም ከመድርክ ግንባታ ዕሳቤ አንጻር አጥኚው ጥሩ ናቸው የሚለዉን በዝርዝር አስቀምጧቸዋል ። በመጀምሪያው ገቢር ትዕይንት አንድ ላይ ያለው ሲናሪና የጎጆ ቤቱ ፤ መደቡ ፤ ዋርካው ቦታውን እና ዘመኑን ታስቦበት

እንዳተስራ ይገልፅልናል ። ወደ ለላኛው ገቢር ሲሸጋገር ሲነሪ ለመቀየር የንበረዉ ፍጥንት የመድርክ ድባቡን አለመቀነሱ እንደ ጥሩ ጎን ማንሳት ይቻላል ። ሌላው ደግሞ ከተዋንያኑ ጀርባ የተሰቀለው ሲናሪ የበአከባቢው ይሚለብሱት፣ የቤት አሰራር እንዴት አንደሆን ያሳየናል ለምሳሌ የሚታዩ ቤቶች የአከባቢውን የቤት አሰራር ይገልፅልናል በቴአትሩ ላይ ያሉት ተዋንያን የለበሱት አልባስት አከባቢውን አለባበስ ይገልፅልናል ። እናም ይህም በመድርክ ግንባታው ከታሪኩ ጋር አዛምዶ ወደ ቦታው ወስዶናል እናም አጥኚው ከብዙ በጥቂቱ ጥሩ ጎን ነው ብሎ ያመናቸዉን በዝርዝር አስቀምጧል ።

ምዕራፍ አራት

4.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ስለ ኪነ—ህንጻ ጥበብ ግንባታ ፣ ስለ መድረክ ግንባታ እና ስለ የ ሚስጥሩ ቴአትር መድረክ ግንባታ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል። የጥናቱ ዋና አላማ ያደረገው "የኪነ—ህንጻ ጥበብ ለቴአትር መድረክ ያለውን አስተዋጾ በሚስጥሩ ቴአትር አስረጂነት ሆኖ ቴአትሩ ከመድረክ ግንባታ አኳያ ሲታይ ደካማና ጥሩ ጎኑን ለማነጻጸር ነው። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ ኪነ—ህንጻ ለቴአትር መድረክ ያለዉን አስተዋጽኦ እንመለከታለን። አጥኚው በዚህ ርዕስ ላይ በኪነ—ህንጻ ጥበብ እና በቴአትር መድረክ ግንባታ መሀል ያለውን አንድነት እና ፋይዳ ቃኝቶታል ።

እንድሁም በ ሚስጥሩ ቴአትር አስረጂነት የመድረኩ ግንባታ ምን ይመስላል ምን አይነት አላባውያን ተጠቅሟል፣ ኪነ—ህንጻስ ለቴአትር መድረክ ያለው አስተዋጽዖ ምንድነው? በማለት በፅሁፍ በመረጃና በምስል መረጃ በማስደገፍ ለማቅረብ ሞክሯል ። በመሆኑም የኪነ—ህንጻ ጥበብ ለቴአትር መድረክ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው እና መድረክ ያለኪነ—ህንጻ ጥበብ መሰራት ሆነ መገንባታ እንደማይችል በ ሚስጥሩ ቴአትር አስረጂነት በማስደገፍ የመድረክ ግንባታውን ችግር አለበት በማለት አጥኚው በጥናታዊ ፅሁፉ አርጋግጧል ።

4.2 የመፍትሄ ሀሳብ

አንድ የመድረክ ንድፉ አውጪ ገና መድረክ ለመገንባት ስነሳና ንድፍ ለማውጣት ሲዘጋጅ የምገነባው መድረክ ከኪነ—ህንጻ ግንባታ አንጻር እንዴት ነው። አላባዎቹስ እንዴት ነው አብሮት የሚሄዱት የሚለውን ነገር በመጀመሪያ ማሰብ አለበት። ካልሆነ ግን የመድረክ ግንባታው ድክመቱ የጎላ የሚሆንበት አጋጣሚ መፈጠሩ አይቀርም። ስለዚህ እያንዳንዱን ሂደት ባለሙያው ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። አንድ መድረክ ግንባታ ብቁ ነው ለመባል የመድረክ ግንባታ አላባዊያንና የኪነ—ህንጻ ጥበብ ግንባታ ማሟላት አለበት። ካሎነ ግን የመድረክ ግንባታው ደካማነው መባሉ አይቀርም እናም መድረክ ሲገነባ ንድፉ አውጪውና የመድረክ ግንባታ ባለሙያው በኪነ ግንባታና በቴአትር መድረክ ግንባታ መሀል ያለውን ቁርኝነት በደንብ ማጤን አለበት። በቴአትር ትምህርት ውስጥ ስል መድረክ ግንባታ እራሱን የቻለ ኮርስ መሰጠት መቻል አለበት።

ምክንያቱም መድረኩ እንዴት ፣ በምን መልኩ ይገንባ ከቴአትር ታረኩ ጋር እንዴት አብሮ ይሄዳል የሚሉትን ነገር ለማወቅ እራሱን የቻለ ኮርስ መሰጠት አለበት። የሀገራችን ቴአትር መድረክ ግንባታ ከአደጉት ሀገራት እኩል ለመሆን ገና ብዙ ያልተሰሩና ያልተዳሰሱ ስራዎች አሉ። ስለዚህ ከቀደሙት እኩል ለመሆን አሁን ያለበትን ችግር በምን እና እንዴት እናስተካክል የሚለው ግንዛቤ በጥልቀት ምረዳት ይኖርበታል ።

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. Architecture means the science of art and the art of construction. In his book Elements of Architectural History, Geomelin Aaron wrote: "The word architecture comes from the Greek word, which is a process called architecton. Its meaning is building foundation (building work or operational composition). The other architecture means a solid construction process. (Geomelin Aaron 21, 1975) (3)"
2. Architecture means strong musical expression. This means that music can provide inner happiness and entertain. The art of architecture is a unique art of construction that not only delights us with our eyes, but also gives us inner appreciation. Therefore, while living his daily life, human being can worry, sad and tired with many things and if he sees and visits architectural construction, perhaps from his fatigue and sadness and anxiety, he will create his inner happiness with these art construction shape and picture. Therefore, it is safe to say that architecture is a powerful expression of music.
3. Architecture consists of different house constructions and has different house shapes which are visually visible construction form and drawing. About Architecture Cevantenia. Janua and Mercia. George (1975) Architecture. They described it as such in their writing. "Architecture is a type of construction that shows the combination of art and creativity in building construction and building content by establishing and defining construction rules. In addition, architecture maintains a serious process of construction. 1975)(4)
4. Architecture is not only a place for human beings but also a great contribution to the glory of a country. For example, it is a form of craft construction that is useful to learn and inform about the history of old houses and buildings. They are the pieces of architecture that are made and built together with various forms of sculpture and woodwork. For example: Phasiledes, Jogol Tower, Lalibela, Axum Monument are mentioned.
5. in his book History of Architectural Stage Theater Technology, Jane Scribery describes the construction of a theater stage. The theater stage or theater was started in Greece. At that time, the reason for the construction of the platform was a religious temple. In connection with that, although the theater was presented in different places, from 1500 B·C onwards, it was thought that the shape of a place of worship (temple) resembled or was related to a place of worship, so the round

stage began to be abandoned in Greece in 1500 B·C. (Jane, Scrubbery, 29, 1985) (5)

6. In 1573-1652, E. Nigo Johan, who designed the stage construction for the first time, designed the stage of the theater. A round stage is a place of performance surrounded by spectators. One of the ways in which the round stage differs from other types of stage, namely the front stage, is the contrast of the position of the stage. Because when a round stage is built, it is lower than the center of the audience. Edwin Wilson , writing the theater experience: "Another point that distinguishes the round stage from the front stage is that it does not use the back stage. Because of this, it is not used in the round stage." (Edwin Wilson , 56, 1976) (6)

ዋቢ መጻሃፍት

- ፋንታሁን እንግዳ ። ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ። አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ቤት ፣ 1993 ።
- ደበበ ሰይፉ። የቴአትር ጥበብ ። አዲስ አበባ ኢትዮጲያ ፣1973 ።
- ዳንኤል ዝውዴ ። የትምህርት ጥናትና ምርምር አተገባበር። አዲሲ አበባ ፣ 1994 ።
- ዶር.ላቢሶ ግ.ደሌቦ ። ሂስቶሪ ኦፍ ኢትዮጵያን አርክቴክቸር ። ፣አዲስ አበባ ፣ 1987 ።
- ዘሪሁን አስፋው ። የስነ_ጽሁፍ መሰረታዊያን ። አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተማይ ቤት ፣ 1992።
- ያለው እዳወቅ ። የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር። አዲስ አበባ ፣አልፋ አሳታሚዎአ ፣ 1998 ዓ.ም
- ፍቃዱ ፍየ እቴነሽ ካሳ ።የእትዮጲያ ቤሄራዊ ቴአትር ታርክ እና የሚሰጣቸዉ አገልግሎት

።አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፣ 2000 ።

- አለም እሸቱ። መሰረታዊ የምርምር እና የዘገባ አጻጻፍ ። አዲስ አበባ ኩራዝ ማተሚያ ፣

1994 ::

- **ሳሙኤል ተስፋዬ ::<u>የመድርክ ጀርባ ጥበባት</u> :: አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጲያ ፣** 2012 ::

- **ፋንታሁን እንግዳ :: <u>የቴውኔት አላባውያን</u> :: አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣** 1992 ::

- Ediwen wilson· The theatre experience· new york· London ,1976.

- Araya, G and wakuma, T. History of ethopian Architecture, (1987)·

- Janne, Scbeiber · History of Architecture Stage Theatre Technology . New York , (1975) .